**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**
**Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)**

የካቲት ፳፱ ቀን ፳፻ ዓም
(ማርች 8/2008)

# የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ድልን ይቀዳጃል

በየዓመቱ የካቲት 29 ቀን የሚከበረው የዓለም የሴቶች ቀን የሀገራችን ሴቶች ያሉበትን የጭቆናና የመከራ ሁኔታ ዳግም በጥሞና እንድንቃኝ የሚያስገድደን ይሆናል፡፡ በቁጥር ብቻ ሳይሆን በገድልም የላቀውን ቦታ ይዘው የቆዩት የኢትዮጵያ ሴቶች በህብረተሰቡ ሊኖራቸው የሚገባውን የክብር ቦታ ሳይዙ እስከዛሬ ቆይተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ መቆም ወይም መለወጥ እንዳለበት ደግሞ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይገባም፡፡

ኢሕአፓ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ አለሴቶች ተሳትፎ ትግላችን ድል አይመታም ማለት ብቻ ሳይሆን ሴቶች መብታቸው ያልተከበረበት ህብረተሰብ ዴሞክራሲያዊ  ሊሆን አይችልም በሚል እምነት ሴቶች በራሳቸው ተደራጅተው ለጋራ ትግሉ ተገቢውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ የመደራጀታቸውን ጥሪ ብቻ ሳይሆን ሂደቱንም አግዟል፡፡ በዚሁ መሰረት ሴቶች በጥናት ክበብና አልፎም በማህበር ተደራጅተው የካቲት አብዮት በፈነዳበት ወቅት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ለትግሉ ለግሰዋል፡፡ የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ በሚል የተቋቋመውን አፋኙ ደርግ ቢያደናቅፈውም ሴቶች    በኢሕአፓ ዙሪያ በመሰለፍ የከፈሉትን መስዋዕትነት ታሪክ የመዘገበው ነው፡፡ በኢትዮጵያ በተካሄዱ ትግሎች ሁሉ ሴቶች ወሳኝና የሚደነቅ ሚና ነበራቸው፡፡ በአድዋ ጦርነት እቴጌ ጣይቱ ስማቸው ገኖ ቢነሳም ከ30 ሺ ያላነሱ ሴቶች በዚያ ጦርነት በልዩ ልዩ ፈርጅ ተሳትፈዋል፡፡
የሙሶሊኒ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ሲወርም ብዙ ሺ ሴቶች በአርበኝነት ታግለዋል፡፡ የውስጥ አርበኞች ድርጅት ዋና አባላት ሴቶች ነበሩ፡፡ በየጦር ሜዳው በተለያየ ደረጃ ከመሳተፋቸው ሌላ በጦር መሪነት ደግሞ እነ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌን፥ ልክየለሽ በያንን፥ አበበች ጨርቆስን፥ ሸዋነሽ አብርሃን፥ ከበደች ስዩምን፥ ቀለመወርቅ ጥሩነህን፥ ባንችይገዙ ኪዳኔን፥ ፀሐይነሽ አበበን፥ ታፈሰች ድፋባቸውንና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአፄው ዘመን ሆነ በዘመነ ደርግ ደግሞ የትግሉ እምብርት በመሆን   የቆራጥነትን ታሪክ አስመዝግበው ያለፉ እህቶቻችንና እናቶቻችን ጥቂት አይደሉም፡፡ በመሆኑም ትግሉ ሊደምቅና ሊጠነክር የሚችልበት ሁኔታ እውን ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ በልዩ ልዩ ጎጂ ባህሎችና እምነቶች የተነሳ ሴቶች የተለየ በደል ሲደርስባቸው ቆይቷል፡፡ መብታቸው ባለመከበሩ ስቃያቸውና በደላቸው ዕጥፍ ድርብ ሆኖ ባጅቷል፡፡ ትግላቸውም ድርብ ድርብርብ መሆን ያለበት በዚሁ ነው፡፡ ከደርግ ዘመን ጀምሮ ባለሥልጣኖች ለሴቶች መብት አፋዊ ድጋፍን ቢሰጡም በተጨባጭ ግን ይህ ነው የሚባል መሰረታዊ ለውጥ ተከስቶ የሴቶች ስቃይ ሲረግብ አልታየም፡፡ ጠባቡና ጨቋኙ የመለስ አገዛዝ በተለይ ሴቶችን በብሄረሰብ ከመከፋፈሉ ሌላ ሴቶችን የግድ ሸቀጥ አድርጎ ለመካከለኛ ምስራቅ ዘረኞች እየሸጠ ያለ ነው፡፡ ዝሙትና ሴትኛ አዳሪነትን አስፋፍቶ፤ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትን ሳይቀር እየደፈረና እያስደፈረ፤ የሴቶችን መብት በህግ መሰረት እንኳን ማስከበርን እምቢ ብሎ አለ ፡፡ ሴቶች ነፃና የራሳቸው የሆነ ድርጅት ሊኖራቸውም አልቻለም፡፡ የወያኔ አገዛዝ በህብረተሰቡ ላይ በፈጠረው ሁለገብ ቀውስ የተነሳም የከተማና በተለይም የገጠር ሴቶች ኑሮ አስከፊ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ብዙ ሺህ ሕፃናት ሴቶች ለባዕዳን በጉዲፈቻ ሲሸጡ የበለጠ ቁጥር ያላቸው ደግሞ መንገድ አዳሪ ሆነው ለጥቃትና ችግር መጋለጣቸው የሚደበቅ አይደለም፡፡ ስለዚህም ከጥቂት የሥርዓቱና የአገዛዙ ሴቶች

በስተቀር የኢትዮጵያ ሴቶች በአብዛኛው መብት አልባ ሆነው እየተሰቃዩ ያሉ ለመሆናቸው ምስክር የሚጠይቅ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሴቶች የዓለም የሴቶች ቀንን ሲያከብሩ ዛሬም ለትግል በመነሳሳት መሆኑ ግልፅ ነው። ሴቶች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉት በቅድሚያ በራሳቸው ሲደራጁና በዚህም አማካይነት የጋራ ትግሉ አካልና አጋር ሲሆኑ ብቻ ነው። የሴቶችን በፆታቸው የመደራጀት መብት በሰበብ አስባቡና በጋራ ትግል ሽፋን ሊክዱ የሚነሱ ወገኖች ለሴቶች ትግልና ድል እንቅፋት ናቸው።
ሴቶች በነፃ ተደራጅተው ለመብታቸው ሊታገሉ ሲነሱ በግድ የሕዝብ የጋራ ጠላት በሆነው አገዛዝ ላይ መነሳታቸው አይቀሬ ይሆናል። ሴቶች አገዛዙና ጠባቦች የዘረጉትን ወጥመድ በጣጥሰው በብሄረሰብ ደረጃ ሳይከፋፈሉ በኢትዮጵያዊ ሴትነታቸው ደረጃ በጋራ ተደራጅተው መነሳት አለባቸው። ሴቶች በትግሉና በሀገራችን ፖለቲካም ተሳትፎአቸውን ማሳደግ ማስፋፋት ይጠበቅባቸዋል። በአንፃሩ ደግሞ ሀገር ወዳጁ ወንድ ሁሉ የሀገራችንን ሴቶች ትግል ከልብ በመደገፍና ከትምክህት ለመፅዳት በመጣር እገዛ ማድረጉ ይጠበቃል። የሴቶችን መብት የሚፃረሩ ጎጂ ባህሎችንም ለማስቀም የጋራ ትግሉ መፋፋም አለበት። በአሁኑ ጊዜ በኤይድስና ሌሎች በሽታዎች ይበልጥ የተጠቁት ሴቶች--ያውም ወጣት ሴቶች--በመሆናቸው ራሳቸውን ከአደጋ እንዲከላከሉም በሁሉ መስክ ማገዝም አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል።

ትግላችን ድልን እንዲቀዳጅ ሴቶች በትግሉ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። ይህ ተሳትፎ ዕውን ይሆን ዘንድም ሴቶች በራሳቸው መደራጀታቸው ወሳኝ ነው። ኢሕአፓ ዛሬም እንደ ትላንቱ የሴቶች መደራጀትና ትግል ጠንክሮ እንዲገኝ በፖለቲካ ፕሮግራሙ እንዳሰፈረው ሁሉ የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደርጋል።

ድል ለኢትዮጵያ ሴቶች ትግል!!

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com